# ሐሜት

ባልንጀሮችዋንና ጎረቤቶችዋን በማማት ጊዜዋን የምታባክን አንዲት ሴት ነበረች። የቤተ ክርስቲያኒቱ ሰባኪ በዚህ ክፉ ስራዋ በብዙ አስቦበት አንድ ቀን ሊገስጻት ቤቷ ድረስ ሄደ። ቤትዋም እንደደረሰ በከረጢት ቋጥሮ የወሰደውን የዶሮ ላባዎች በሜዳ እንድትበትን ነገራት። እርስዋም በነገሩ በመደነቅ እንዳላት አደረገች። የዶሮ ላባዎቹን ለነፋስ ሰጠች። ነፋሱ ላባዎቹን በየስፍራው አሰራጨ። ከዚያም ቀጥሎ ላባዎቹን እንድትሰበስባቸው ጠየቃት። ሴቲቱም የማይቻላት መሆኑን ገለጸች። ሰባኪው በዚህን ጊዜ ሊያስተምራት የፈለገውን ነገር እንዲህ ሲል ተናገረ። በየስፍራው የተሰራጩትን ላባዎች መሰብሰብ እንደማይቻል ሁሉ እንደዚሁም በሐሜት የፈጸምሽውን ጉዳት ሁሉ መመለስ አይቻልም። ሴቲቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ምላሷ ክፉ እንደሆነ ለመገንዘብ በቃች። (1ኛ ጢሞ. 3:11)

አንባቢ ሆይ:- አንተም ሰው አምተህ እንደሆነ እስቲ አስታውስ። በሐሜትህ ሌላውን ሰው ጎድተህ አታውቅምን? በክፉ ንግግርህስ በወዳጆችህ መካከል መለያየትን ፈጥረህ አታውቅምን? በሌሎን

2፡21 እና በ1ኛጴጥ.2፡5 እግዚአብሔር አንድ ቅዱስ ቤት እንደሚገነባና ድንጋዮቹም እኛ ክርስቲያኖች እንደሆንን ይነግረናል። በክፉ ንግግር እርስ በርሳችን የምንጎዳዳ ከሆንን ጌታችን የሚገነባውን ቤት ማፍረሳችን አይደለምን?

እርስ በርሳችን እንዳንፈራረድ ወይም እንዳንተማማ እግዚአብሔር ብዙ ትዕዛዛትን ሰጥቶናል። (ማቴ.7፡1-2) ስለ አንዱ ወንድማችን ክፉ ስንናገር ትዕዛዙን መጣሳችንና ለጌታም አለመታዘዛችን ነው። (ያዕ.4፡11-12) ብዙዎች ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛቸው ምክንያት ሰላምና ደስታ የላቸውም። (1ኛጴጥ.3፡10-11)

## ስለ ሐሜት ክፋት እስቲ እንመርምር።

1ኛ. ለሐሜተኛው፡- ለእግዚአብሔር የማይታዘዝ ነው፤ እርሱ ረክሷል። (ያዕ.1፡26) መንፈሱ መጥፎ ነው። ከሚያማቸው ሰዎች ተለይቷል።(ምሳ.16፡27-28፤ መዝ.50፡16-21)

2ኛ. ሐሜት ለሚሰማ፡- የረከሰ ይሆናል፤ ከታማው ሰው ጋር ይጣላ ይሆናል፤ መንፈሱ ይበላሻል፤ ስለታማው ሰው የሰማውን ክፋት ሊረሳ አይችልም።

3ኛ. ለታማው ሰው፡- ስሙ ተበላሽቷል፡ ምስክርነቱ ተጎድቶአል ከወንድሞቹ ተለይቷል፡ ለእግዚአብሔር የሚሠራው ስራ ይደናቀፋል፡፡

4ኛ. ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ።

ሕጉ ተጥሶበታል(ቲቶ.3፡1-2) ተከታዮቹ ተለይተውታል፤ ልቡ አዝኖአል፤ ስራው ታግዶአል ዓላማው አልተፈጸመም።

ከሐሜት መልካም ነገር ይገኝ እንደሆን እስቲ መርምርና ራስህን እንዲህ ብለህ ጠይቅ፡- «ምላሴ በዚህ በሰይጣን ሙያ እንዲውል ለምን አደርገዋለሁ?»

## ስለ ሐሜት እስቲ ጥቂት ነገሮችን እንመርምር

1ኛ. የምንሰማቸው ብዙ ነገሮች ውሸት ይሆናሉ ሰይጣን ራሱ ብዙ ውሸት ይናገራል። (ዮሐ.8፡44) ነገሩን የሰማነው፡- ከውሸተኛ ምንጭ ይሆናል።

2ኛ. ሐሜቱ እውነት ቢሆንም እየደጋገሙ መናገር ዋጋ የለውም ሰውን ለመውቀስ ስታስብ ራስህን እንዲህ ብለህ ጠይቅ «አምላኬ በዚህ ነገር ይደሰታልን ? ያላመኑት እንዲድኑ ይረዳልን ?»

አረ ለመሆኑ ክርስቲያኖች ለምን ያማሉ ? ከሚያሙት ሰው ራሳቸውን ለማብለጥ ከፍ ለማድረግ ሲፈልጉ አይደለምን? ከቅናትና ከምቀኝነት የተነሳ ሌሎቹንም ለመጉዳት ከሚያስቡት ጥላቻ የተነሳ ያማሉ።(ያዕ.3:1-11) አንዳንዶች ክርስቲያኖች ደግሞ በልማድ ያማሉ።

እንግዲህ ምን እናድርግ? የሚከተሉትን ደንቦች መታዘዝ ከሐሜት እንድንርቅ ይረዳናል።

1ኛ. በሌሎች ላይ የምታየውን ወይም ያየህ የሚመስልህን ክፋት በጭራሽ አታውራ።
2ኛ. ስለ ሌሎች የምትሰማውን ክፋት ከቶ አትድገመው።
3ኛ. የምትሰማውን ሐሜት እርሳው። በሐሜተኛውም ቂም አትያዝ።
4ኛ. እንደዚህ ያለውን ነገር ስትሰማ ችላ ማለት ቢያስፈልግም በመዝለፍ አስቀረው።

5ኛ. በክርስቶስ ኃይል እንደዚህ ያሉትን አሳቦችና ቃሎች እንድትንቃቸው ንጹህ ልብ እንዲሰጥህ እግዚአብሔርን በጸሎት መጠየቅ ነው። (ቆላ።4:6)

ኢስ.አይ.ኤም.ማተሚያ ቤት ታተመ።